ቁጥር OFAGF-04,1/4/12
ቀን 14/07/2012

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ለክቡር አቶ አወል ወግሪስ

የአሶሳ ዩኒቨርስቲ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ ፡ <u>የአሶሳ ዩኒቨርስቲ የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየትን ይመለከታል፣</u>

ከላይ በርዕሱ የተጠቀሰው ኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 09 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና 49 ገጽ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልጻለን ።

ከሰላምታ ጋር

መሰረት ዳምጤ
የኦዲት ዘርፍ ም/ዋና ኦዲተር

<u>ግልባጭ፣</u>

የአሶሳ ዩኒቨርስቲ
(58 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና
18 ገጽ የሂሳብ ሪፖርቶች)
<u>አሶሳ</u>

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ

የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርስቲ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡ ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርሲቲው ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድርሂሳብሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

<u>ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣</u>

የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

<u>የገቢ ሂሳብ፣</u>

1. በዩኒቨርስቲው ውስጥ የተቋቋመው የሀብት ልማትና ገቢ ማመንጫ ዳይሬክቶሬት በ2011 በጀት ዓመት ከእንስሳት ተዋፅኦ እና ከሰብል ምርት ብር 107,470.00፣ ከተረፈ ምርቶች ብር 114,657.20 እና የተለያዩ አገልግሎት የሚሰጡ ቤቶችን በማከራየት ብር 673,840.00 በድምር ብር 895,967.20 በበጀት ዓመቱ እንደሰበሰበ ለዩኒቨርስቲው ለቢዝነስ ልማት ም/ፕሬዝዳንት በደብዳቤ ቁጥር አሶ/ዩ/ገቢ/ማ/173/11 በቀን 28/10/2011 ሪፖርት የተደረገ ቢሆንም የተሰበሰበው እያንዳንዱ ገቢ ሰነድ ተለይቶ ወደ አይቤክስ/IBEX ያልተመዘገበ በመሆኑ የገቢውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም::

2. ዩኒቨርስቲው ከመማር ማስተማር የሚሰበስበውን ገቢም ሆነ ለመምህራን ክፍያ እና ገቢውን ለማመንጨት ያወጣውን ሌሎች የወጪዎች ሰነድ ተለይተው በአይቤክስ/IBEX ያልተመዘገቡ በመሆኑ የወጪውንም ሆነ የገቢውን ሂሳብ ሪፖርት ያላደረገ በመሆኑ የተዘጋጀው የሂሳብ ሪፖርት የዩኒቨርስቲውን የተሟላ የሂሳብ እንቅስቃሴ እንዳያሳይ አድርጓል፡፡
3. ዩኒቨርሲቲው በድምሩ ብር 28,140.55 የሥራ ግብር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ሳይቀነስ ክፍያ የፈፀመ በመሆኑ መንግስት የሚያገኘውን ገቢ እንዲያጣ አድርጓል፡፡
4. በድምሩ ብር 314,231.59 የጉዳት ካሣ /Liquidation Damage/ ገቢ አለመደረጉ እና የሁለት ግንባታ ፕሮጀክቶች በውላቸው መሰረት በተያዘለት የጊዜ ገደብ መጠናቀቅ ሲገባቸው ያልተጠናቀቁ/የዘገዩ በመሆኑ ለመንግስት ገቢ መሆን የነበረበት እንዳይገባ ከማድረጉም ባሻገር አፈጻጸሙ ለብልሹ አሰራር በር እንዲከፈት አድርጓል፡፡

<u>የወጪ ሂሳብ፣</u>

5. ዩኒቨርስቲው ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ሳይገኝ፣
   - ዩኒቨርሲቲው በራሱ የክፍያ ተመን በማውጣት ለአሶሳ አጠቃላይ ሆስፒታል 7 ሐኪሞች የደመወዛቸውን 100%፣ እንዲሁም ለፓዊ አጠቃላይ ሆስፒታል 25 ባለሙያዎች የደመወዛቸውን 75% በየወሩ ክፍያ እየፈፀመ በመሆኑ በድምሩ ብር 675,357.75 ከመንግስት መመሪያ ውጭ የተከፈለ መሆኑ፣
   - በ2010 በጀት ዓመት በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ለተካሄዱ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ዘርፍ ስራዎች ግምገማ ላካሄዱበት በሚል ለ50 አባላት ዩኒቨርሲቲው በራሱ የክፍያ ተመን በማውጣት በቀን 12/01/11 በድምሩ ብር 231,000.00 የሙያ ክፍያ በሚል ከመንግስት መመሪያ ውጭ የተከፈለ መሆኑ፣

   በአጠቃላይ ብር 906,357.75 ያለአግባብ ከደንብና መመሪያ ውጭ ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ በመሆኑ የህግ ጥሰትን ከማስከተሉም በተጨማሪ የመንግስት ውስን ሀብት አለአግባብ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡
6. ዩኒቨርስቲው በድምሩ በብር 1,528,275.00 ከወንደሰን ዝቁ መንግስቱ እህል ንግድ ለቀረበለት አተር ክክ፣ ምስር ክክ እና ሩዝ ክፍያ ሲፈፀም ከተቀመጠው የዋጋ ማስተካከያ በላይ አለአግባብ ብር 275,927.00 በብልጫ ክፍያ የፈፀመ በመሆኑ በዚህ ምክንያት የዩኒቨርስቲው የወጪ ሂሳብ ከፍ እንዲል አድርጓል፡፡

7. ዩኒቨርሲቲው እንዲከፈል የተመደበውን አበል ለእያንዳንዱ ቀን እንደሚከፈል ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ከግንቦት 24 እስከ 25/2010 ዓ.ም እና ከግንቦት 26 እስከ 27/2010 ዓ.ም ለአራተኛ ጊዜ በሀገር አቀፍ ደረጃ እና ለስምንተኛ ጊዜ በዓለም አቀፍ የምርምር ጉባኤ ላስተባበሩ 70 ሰራተኞች የምሳ አበል ሲከፈል የ4 ቀን ብቻ ብር 14,000.00 (4*50*70) መከፈል ሲገባው፣ ለ31 ሰራተኞች ለእያንዳዳቸው የ10 ቀን የምሳ አበል ብር 15,500.00 (10*50*31) እና ለ39 ሰራተኞች ለእያንዳዳቸው የ20 ቀን የምሳ አበል ብር 39,000.00 (20*50*39) በድምሩ ብር 54,500.00 የተከፈለ በመሆኑ ብር **40,500.00** በብልጫ መከፈሉን፣
- በቀን 28/01/11 ለኢትዮጵያ አየር መንገድ በተፃፈው ደብዳቤ በ01/02/2011 ከአሶሳ አዲስ አበባ እንደሚሄዱና በ04/02/11 ከአዲስ አበባ አሶሳ እንደሚመለሱ ተጠቅሶ የአውሮፕላን ትኬት የተቆረጠላቸው ሲሆን፣ በዚህ መሰረት ጉዞን ጨምሮ ለ4 ቀናት ብቻ ብር 19,436.00 መከፈል ሲገባው፣ ለ7 ተሳታፊዎች የ15 ቀን ብር 13,020.00 (7*15*124)፣ ለ3 ተሳታፊዎች የ10 ቀን ብር 17,250.00 (3*10*575) እና ለ11 ተሳታፊዎች የ10 ቀን ብር 22,660.00 (11*10*206) በድምሩ ብር 52,930.00 የተከፈለ በመሆኑ ብር **33,494.00** በብልጫ መከፈሉን፣
- የተለያዩ ቦታዎችን ለመጎብኘትና የኢንዱስትሪ ትስስር ለመፍጠር በጉብኝቱ ለሚሳተፉ ለ40 አመራሮች አበል እንዲከፍል የታዘዘ እና ጉብኝቱ ከየካቲት 20 እስከ 23/2011 ዓ.ም ቀን ብቻ በመሆኑ የ4 ቀን አበል ብር 25,600.00 (4*160*40) መከፈል ሲገባው፣ የ8 ቀን አበል ብር 51,200.00 (8*160*40) የተከፈለ በመሆኑ ብር **25,600.00** በብልጫ መከፈሉን፣
- በዩኒቨርስቲው የመሰብሰቢያ አዳራሽ ከሰኔ 25 እስከ 26 /2011 ዓ.ም ለተካሄደው የጥናትና ምርምር ውይይት የዩኒቨርስቲው ሰራተኞች እና ከአሶሳ ከተማ ባለድርሻ አካለት ለተሳተፉ 176 ተሳታፊዎች በቀን ብር 50.00 ሂሳብ ለ10 ቀን ብር **88,000.00** (176*50*10) ያለአግባብ ከመመሪያ ውጭ የተከፈለ መሆኑን፣
- ዩኒቨርሲቲው በተለያዩ ቀናት የትራንስፖርት አገልግሎት ግዥ ሲፈፅም በተማሪዎችና በስታፍ ሰራተኞች ቁጥር ልክ መሆን ሲገባው የትምህርት

ክፍሉ ከሳከው ቁጥር በላይ ውል በመግባት ክፍያ እየተፈፀመ በመሆኑ በድምሩ ብር 72,853.50 ያለአግባብ በብልጫ ወጪ መደረጉን፣

- ለዊንታ ህትመት ስራ ድርጅት በብልጫ ብር 6,653.44 ያለአግባብ ወጪ መደረጉን፣
- ዩኒቨርሲቲው በጨረታ ተወዳድሮ ካሸነፈው አቅራቢ ከዋዩ ጉድሩ ኢንተርናሽናል ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ለቀረበለት የአይ.ሲ.ቲ ዕቃ በብር 881,999.95 ዋጋ ያቀረቡ ሲሆን፣ ምዝገባ ሲከናወን በብር 897,339.07 ክፍያ በመፈፀሙ በብልጫ ብር 15,339.12 መከፈሉን፣

በጠቅላላው ብር 282,440.06 ያለአግባብ ከመመሪያ ውጭ በብልጫ ተከፍሎ በመገኘቱ በዚህ ምክንያት የዩኒቨርስቲው የወጪ ሂሳብ ከፍ እንዲል አድርጓል።

8. ዩኒቨርሲቲው በአጠቃላይ ብር 56,784.00 ከሚመለከታቸው የስራ ክፍል ሠራተኞች በስራ ላይ ስለመሆናቸው ማስረጃ/ማረጋገጫ ሳይቀርብ ሥራ ለለቀቁ ሠራተኞች በየወሩ ደመወዝ ክፍሎ በመገኘቱ አለአግባብ የዩኒቨርስቲው ወጪ ከፍ እንዲል አድርጓል።
9. ዩኒቨርሲቲው ለተለያዩ ድርጅቶች በአጠቃላይ ብር 319,936.16 የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሳይቀረብ ክፍያ ፈፅሞ በመገኘቱ የወጪ ሂሣብን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም።
10. ዩኒቨርሲቲው በድምሩ ብር 28,817,598.17 ከተደለደለው የሂሳብ መደብ ውጭ የተመዘገቡ መሆኑ እና ከዚህ ሂሳብ ውስጥ በምግብ ያልተያዘው ወጪ ብር 8,974,435.17 ተማሪዎች ከተመረቁ በኃላ ለመንግስት በሚከፍሉት የወጪ መጋራት ክፍያ ላይ የማይታይ በመሆኑ መንግስት ላወጣው ከተማሪዎች መሰብሰብ የሚገባውን ገንዘብ የማይሰበሰብ መሆኑ እና ወጪው ያለሂሳብ መደቡ ተመዝግቦ ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን፣ የበጀት ዝውውር በማድረግ በትክክለኛው የሂሳብ መደብ መመዝገብ ሲገባው፣ የበጀት አዋጁን በመጣስ በድምሩ ብር 8,974,435.17 ከተደለደለው በጀት በላይ የበጀት ዝውውር ሳይደረግ ወጪ በማድረግ ባልተፈቀደ የሂሳብ መደብ ተመዝግቦ በመገኘቱ የዩኒቨርስቲው ሂሳብ እንዲዛባ አድርጓል።
11. ዩኒቨርስቲው ግዥዎችን ሲፈፅም የግዥ ደንብ፣ መመሪያውንና በአዋጁ መሠረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፦
    - በጠቅላላው የብር 4,341,818.41 የዋጋ ማወዳደሪያ ቀርቦ ውድድር ሳይደረግ ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ አገልግሎቱን ከሚሰጠው ድርጅት እና ግለሰብ ግዥ የፈጸመ በመሆኑ፣

- በጨረታ ካሸነፈው መገዛት ሲገባው በዋጋ ማወዳደሪያ የግዥ ዘዴ በመግዛቱ በጠቅላላ ብር 200,485.00 መንግስት አለአግባብ እንዲያወጣ የተደረገ በመሆኑ፣
- ግዥዎች በሚፈጽሙበት ጊዜ አሰባስቦ በግልጽ ጨረታ መግዛት ሲገባው በድምሩ 3,781,490.57 ከተለያዩ ድርጅቶች በዋጋ ማወዳደሪያ ቆራርጦ ግዥ የፈፀመ መሆኑን፣

በአጠቃላይ ብር 8,323,793.98 በግዥ ደንብ፣ መመሪያ እና አዋጅ መሠረት ተፈፃሚ ባለመሆኑ ቁጠባን የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ አልተቻለም።

12. ዩኒቨርሲቲው የበጀት ዓመቱን ክፍያ በበጀት ዓመቱ ውስጥ መክፈልና ማወራረድ ሲገባው በድምሩ ብር 10,254,178.62 በ2010 በጀት ዓመት መከፈል እና መወራረድ የሚገባው በ2011 በጀት ዓመት ላይ ክፍያ የተፈፀመና የተወራረደ መሆኑን ተረጋግጧል። በዚህ ምክንያት የሂሳብ ሪፖርቱ ላይ የተመለከተው ትክክለኛውን የበጀት ዓመቱን ወጪዎች እንዳያመለክት አድርጓል።
13. ዩኒቨርሲቲው ለተማሪዎች ምግብ ወጪ ከመደበኛ በጀት መሸፈን ሲገባው፣ ከመመሪያ ውጭ ከውስጥ ገቢ ላይ ለተማሪዎች የምግብ ግብአት የሚውል ግዥ አከናውኖ በድምሩ ብር 1,189,184.80 ክፍያ የፈፀመ መሆኑን እና ይሄው ወጪ የተደረገው ገንዘብ ወደ አይቤክስ በወጪ ተመዝግቦ ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑን እና በተጨማሪ ተማሪዎች ከተመረቁ በኋላ ለመንግስት በሚከፍሉት የወጪ መጋራት ክፍያ ላይ የማይታይ በመሆኑ መንግስት ላወጣው ከተማሪዎች መሰብሰብ የሚገባውን ገንዘብ እንዳይሰበሰብ የሚያደርግና የመደበኛውን የወጪ ሂሳብ ዝቅ ተደርጎ በሪፖርት እዲታይ አድርጓል።
14. ዩኒቨርሲቲው በገበያ ጥናት በተደረገበት ዋጋ ግዥ መፈፀም ሲገባው በተጋነነ ዋጋ ግዥው በመፈፀሙ በአጠቃላይ ብር 119,580.18 በብልጫ ክፍያ የፈፀመ በመሆኑ አለአግባብ የዩኒቨርስቲው ወጪ ከፍ እንዲል አድርጓል።
15. ዩኒቨርሲቲው በድምሩ ብር 732,320.50 በመመሪያው መሰረት በአግባቡ ጨረታ ወጥቶና ውል ተፈጽሞ ግዥው የተከናወነ ለመሆኑ እና በመንግስት የውሎ አበል መመሪያ መሰረት የተከፈለ ስለመሆኑ የተሟላ የወጪ ማስረጃዎች ለኦዲት ባለመቅረባቸው የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም።

16.ዩኒቨርሲቲው ስራው ከተቋረጠ ግንባታ ከወሰዱት ቅድሚያ ክፍያ ውስጥ ብር 2,892,735.11 ተመላሽ ያልተደረገ በመሆኑ ደንብና መመሪያ ተፈፃሚ አለመደረጉንና ለመንግሥት ገቢ የሚደረገውን ሂሳብ አለአግባብ በዚሁ መጠን እንዲያንስ አድርጓል።

የተሰብሳቢ ሂሳብ፣

17.ዩኒቨርስቲው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከሚታየው ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ በድምሩ ብር 54,080,131.38 እስከ 2011 በጀት ዓመት መጨረሻ መወራረድ ሲገባው፣ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩን፣

የተከፋይ ሂሳብ፣

18.ዩኒቨርሲቲው በገባው ግዴታ መሰረት በወቅቱ መክፈል ሲገባው ከመደበኛ በጀት በድምሩ ብር 31,325,148.73 በተከፋይ ተይዞ የሚታይ መሆኑን፣

በጀት፣

19.ዩኒቨርስቲው ከመደበኛ በጀት በድምሩ ብር 1,412,334.94 የበጀት ዝውውር ሳይደረግ ለሂሳብ መደቡ ከተፈቀደው በጀት በላይ ተጠቅሞ በመገኘቱ የወጪ ሂሣብ በጀቱ በዕቅዱ መሠረት አለመፈፀሙ የዩኒቨርስቲውን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ ያደርገዋል።

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 19 በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የዩኒቨርስቲውን የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም።

ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፣

ምንም እንኳን በሰጠነው አስተያየት ላይ ለውጥ ባያስከትሉም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊደረግባቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል።

- ዩኒቨርሲቲው ከሚያስገነባቸው ግንባታዎች መካከል የመምህራን መኖሪያ ህንጻ እና የተማሪዎች መማሪያ ክፍሎችን ለማስገንባት በወጣው ግልፅ ጨረታ ተወዳድሮ በብር 286,622,093.00 አሸናፊ ለሆነው ስራ ተቋራጭ በመመሪያው መሰረት የጠቅላላ ክፍያው 20 በመቶ ብር 57,324,418.60 ቅድመ ክፍያ እንዲፈፀም ተጠይቆ ነገር ግን ካለው የጥሬ ገንዘብ እጥረት የቅድመ ክፍያውን 50 በመቶ ብቻ እንዲከፈል በታዘዘው መሰረት ብር 28,662,209.30 ክፍያ የተፈፀመ ቢሆንም ከዩኒቨርሲቲው ፕሮጀክት

ፅ/ቤት በተገኘ መረጃ መሰረት ተቋራጩ የስራ ቦታ የተረከበ እና ቅድመ ክፍያ የተፈፀመለት ቢሆንም አዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት እስከ 29/04/2012 ድረስ ስራ ያልጀመረ መሆኑን፣

- ዩኒቨርሲቲው ከኪሮስ ሃድጉ ጠቅ/ህ/ስራ ተቋራጭ ጋር ለውጥ ስራ ውል በፌዝ-5 ሎት 01 የአጥር እና ዋና መግቢያ በር የጥበቃ ቤት ተያያዥ ስራዎችን ለመገንባት በቀን 30/02/2011 ውል የተፈጸመ ሲሆን፣ ውሉ የሚጠናቀቅበት ጊዜ ውሉ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ባሉት 5 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ስራውን ጀምሮ በ180 ቀን /በስድስ ወር/ ከህዳር 01/2011 እስከ ሚያዝያ 30/2011 ባለው ጊዜ ውስጥ ስራውን አጠናቆ ማስረከብ ሲገባው፣ ስራው ማለትም Variation work 03 electrical በብር 4,164,702.85 እና Supplementary work guard house በብር 2,640,538.00 በድምሩ ብር 6,805,240.85 እስከ ሰኔ 30/2011 ድረስ ሳይጀመር የቆየ መሆኑን፣
- ዩኒቨርስቲው ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው በጀት አጠቃቀም በየሂሳብ መደቦቹ ሲታይ ከ10% በላይ ከመደበኛ በጀት በድምሩ ብር 5,727,664.50 እና ከካፒታል በድምሩ ብር 128,930,325.51 በጠቅላላው ብር 134,657,990.01 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑን፣

ሌሎች ጉዳዮች፣

- የዩኒቨርስቲው የንብረት አመዘጋገብ፣ አያያዝ እና አጠባበቅ አጠቃላይ ሲታይ የመንግስት ንብረት በጥንቃቄና በአግባቡ የማይያዝ፣ የአጠቃቀም ጥንቃቄ የማይደረግ፣ እንዲሁም የመቆጣጠር እና የአገልገሎት ላይ በማይውልበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ የማይወገዱ መሆኑን፣
- የዩኒቨርሲቲው ተሽከርካሪ መኪናዎች የነዳጅ አጠቃቀምና_አስተዳደር ሲታይ፡-
    - በ2011 በጀት ዓመት የተሽከርካሪ መረጃ አያያዝ በተመለከተ ተሽከርካሪዎቹ በኪ/ሜትር የሚጠቀሙት ነዳጅ በአግባቡ እየተመዘገበ ሂሳቡ እየተሰላ እና እየተቀናነሰ የማይረጋገጥ ስለሆነ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያላስቻለ መሆኑን፣
    - የሰሌዳ ቁጥር 4-17012 ሰንሎንግ አውቶቡስ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር /ሊብሬ/ የሌለው መሆኑን፣
    - አንድ ትራክተር ተሽከርካሪ የሰሌዳ ቁጥርና የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር /ሊብሬ/ የሌለው መሆኑን፣

- የዩኒቨርሲቲው የውስጥ ኦዲት አሰራር ሲታይ በስራ ክፍሉ መዋቅር መሰረት 13 የሰው ኃይል እንደሚያስፈልገው የተገለጸ ቢሆንም፣ በስራ ክፍሉ 4 የሰው ኃይል ብቻ ያለው በመሆኑ፣ 9 የስራ መደብ ያልተሸፈነ እና የተፈጠረውን የባለሙያ እጥረት እንዲሟላ ባለመደረጉ በዕቅዱ መሰረት እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ሪፖርቶች ወቅታቸውን ጠብቀው እንዲቀርቡ ለማድረግ ያልቻለ መሆኑን፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት